# የኢትዮጵያ የስደት መንግስት፤ ከህሳቤ ወደ ተግባራዊነት

ነሐሴ 14፣ 2007

የኢትዮጵያ የስደት መንግስት መመስረት አስፈላጊነት ላለፉት ሁለት አስርት አመታት፣ በተለይ ደግሞ የግንቦት 1997 ዓ.ም. ሃገራዊ ምርጫን የህወሃት/ኢህአዴግ ስርዓት በጠመንጃ አፈሙዝ ከህዝብ መንጠቁን ተከትሎ ውይይትና ክርክር ሲደረግበት ቆይቷል። የተሰረቀውን የህዝብ ድምፅ ለማስመለስ የተለያዩ ግለሰቦችና ድርጅቶች የተለያየ የትግል ስልት መከተልን መርጠዋል። አንዳንዶች የትጥቅ ትግል ሲመርጡ፣ ሌሎች የምርጫ ፖለቲካን ገፍተውበታል። የአፓርታይዱ ወያኔን አምባገነን ስርዓት አስወግዶ ሁሉን አቀፍ ህዝባዊ የሽግግር መንግስት ለማቋቋም እስካሁን ያልተሞከረ መንገድ ቢኖር የፓርቲ ፖለቲካን ወደ ጎን በመተው ባለድርሻ አካላትን ሁሉ ያሳተፈ የስደት መንግስት መመስረት ነው።

ይህን ሃሳብ ወደ ቀጣይ ምዕራፍ ለማሸጋገር ሐምሌ 2012 እ.አ.አ. አያሌ ኢትዮጵያውያን በዳላስ ቴክሳስ በመሰባሰብ የኢትዮጵያ የሽግግር ምክር ቤት መስርተዋል። የሽግግር ምክር ቤቱም ላለፉት 3 ዓመታት ሃሳቡን ለማስረፅና ስምምነት ለመድረስ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በርካታ ስብሰባዎችና የምክክር ጉባዔዎች አካሂዷል።

ባሳለፍነው ወር ሐምሌ 2015 የኢትዮጵያ ብሄራዊ የሽግግር ምክር ቤቱና የኢትዮጵያ ወጣቶች ብሄራዊ ንቅናቄ ከተለያዩ የድርጅቶች ተወካዮችና ታዋቂ ግለሰቦች ጋር ለሁለት ቀናት በዋሽንግተን ዲሲ ውይይት ካደረጉ በኋላ የኢትዮጵያ የስደት መንግስት አደራጅ ኮሚቴ ለማቋቋም ተስማምተዋል።

በአሁን ወቅት የኢትዮጵያ የስደት መንግስት አደራጅ ኮሚቴ በመመስረት ላይ ይገኛል። የመጀመሪያ መዋቅሩ ተዘጋጅቷል። የኮሚቴው ተቀዳሚ ስራ የሚሆነው፤ 1) የኢትዮጵያ የስደት መንግስት መመስረት አስፈላጊነትን ለህብረተሰቡ ግንዛቤ ማስጨበጥ፣ 2) አስፈላጊ የሆኑ ህዝባዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ዲፕሎማሲያዊና የፋይናንስ ድጋፎችን ማሰባሰብ 3) የስደት መንግስቱን መሰረት መገንባት።

የስደት መንግስት ምስረታው ብዙ ደረጃዎች ይኖሩታል። የኢትዮጵያን ህዝብ ድጋፍ ለማግኘት በጣም በጥንቃቄ ታቅዶ ጠንካራ ስራ መስራት እንደሚያስፈልግ ኮሚቴው ይረዳል። በተጨማሪም ዘርፈ-ብዙ ስራዎችም እንዳሉት ይገነዘባል። በሚቀጥሉት ቀናትና ሳምንታት አደራጅ ኮሚቴው የነደፋቸውን እቅዶች ለህዝብ ይፋ በማድረግ የተለያዩ ተግባራትን ያከናውናል።

የኢትዮጵያ የስደት መንግስት የመጨረሻ ግብ የሚሆነው ኢትዮጵያ ውስጥ የተረጋጋ፣ ሰላማዊና ወደትክክለኛ ዲሞክራሲያዊ ሽግግር መኖሩን ማረጋገጥ ነው። ከዚህ በፊት ያልታቀደ የስርዓት ለውጥ የሚያስከትለውን ቀውስ አይተናል። ለዚህ ደግሞ ሃገራችንን መመልከት በቂ ነው። በአሁን ወቅት በሶሪያና ሊቢያ እየሆነ ያለውን መመልከትም እንችላለን። ኢትዮጵያ ውስጥ ፈጠነም ዘገየም ለውጥ መምጣቱ የማይቀር ነው -- ምክንያቱም አምባገነን ስርዓትን ለመታገል  ህዝብ በየትኛውም ሀገር ቢሆን ማመጹ ስለማይቀር። በተቻለ መጠን ሌላ ቀይ ሽብር፣ ሌላ አፓርታይድ ስርዓት፣ ሌላ የህዝብ እልቂት በሀገራችን እንዳይከሰት የሚመጣው ለውጥ በሰላማዊ ሂደት እንዲያልቅ እንፈልጋለን።

የታቀደ፣ የተደራጀና ሠላማዊ ለውጥ ኢትዮጵያ ውስጥ እንዲመሰረት በሚደረገው ጥረት ሀገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን ሁሉ እንድትሳተፉ ጥሪያችንን እናስተላልፋለን!

ለግንኙነት በኢሜል፤

contact@etntc.org ወይም ethioyouthmov@gmail.com

# Ethiopian Government In Exile: From Idea to Reality

Date: August 20, 2015

The idea of forming the Government of Ethiopia in Exile (GEE) has been discussed and debated for the past two decades, and particularly since January 2006 when the TPLF regime stole the May 2005 elections at the barrel of the gun. Different organizations and individuals took various routes to restore the will of the people that was expressed through the ballot box in 2005. Some argued for and chose to raise arms. Others dug in and tried to give electoral politics further try. What has not been tried yet in the struggle to remove the apartheid dictatorship in Ethiopia and replace it with an all-inclusive transitional government is setting aside party politics and bringing all stakeholders under an all-inclusive government in exile.

To take the idea to the next level, in July 2012, several Ethiopians had gathered in Dallas, Texas, and formed Ethiopian National Transitional Council (ENTC). For the past 3 years, ENTC has held numerous town hall meetings and consultative conferences to refine the idea and reach a consensus among various stakeholders.

Last month, July 2015, ENTC and Ethiopian National Youth Movement (ENYM) have decided to take the idea to the next level after a two-day consultation with various stakeholders. They have agreed to create the Government of Ethiopia in Exile Organizing Committee (GEEOC).

Currently, the GEEOC is in the process of being formed. The initial structure has been set up. Its primary tasks include: 1) create public awareness for the need to form Ethiopian government in exile, 2) gather the necessary public, political, diplomatic, financial and material support, and 3) build the foundation.

Creating the government in exile has multiple phases. The organizers understand that it is a complicated process that requires careful planning and hard work in order for it to gain the support of the Ethiopian people. In the coming days and weeks, GEEOC will make detailed plans available to the public and carry out various activities.

The GEE's ultimate goal is to ensure that there will be a smooth and peaceful transition to genuine democracy in Ethiopia. We have witnessed the devastating effects of unplanned changes of regime. We should look no further than our own country. Let's also observe what is currently going on in Syria and Libya. Change is inevitable in Ethiopia because people anywhere rise up against tyranny sooner or later. We want that change to take place in a peaceful manner as much as possible, thus averting another Red Terror, another transition to an apartheid system, and a further threat to the well-being of Ethiopia.

Join us. Take part in the effort to bring a planned, organized and peaceful change in Ethiopia.

Contact Email:

contact@etntc.org or ethioyouthmov@gmail.com